# የአብይ ጦርነት

የማይቆረጠም ፣ የብረት አሎሎ
ፅንፈኛውን ሃሳብ ፣ አንጓሎ አንጓሎ
ትግሉ ሳይጀመር ፣ ገና "ሀ" ተብሎ
በሃሳብ ልዕልና ፣ ከሁሉም አይሎ
አብይና ለማን ፣ በዝረራ ጥሎ
ሴራና ደባውን ፣ አይሞቱ ሞት ገሎ
ከነ ክንብንቡ ፣ የኦነግ ደበሎ
        ህልማቸውን ቀብሮ ፣ ላያገግም በቅሎ
        እንጦሮንጦስ ላከው ፣ ሄደ ተንከባሎ ።

እምነት ፣ ማተብ የለው ፣ በቃሉ እማይረጋ
ትላንትና ፣ ያለውን ፣ የሚሽር ሲነጋ
በለበጣ አንድነት ፣ ወዷት ፣ ጠጋ ጠጋ
የዘውግ አካሄዱ ፣ መስሎት ፣ አልጋ ባልጋ
የሌሎቹን ውድቀት ፣ ፈጥኖ ከዘነጋ
        ፊቱ የተደቀነው ፣ ካልታየው አደጋ
        በውርደት በቅሌት ፣ ይከፍላታል ዋጋ ።

ገጀራና ቆመጥ ፣ የያዘ ካልሆነ
የሰላም ታጋዩን ፣ ፈርቶ ከበተነ
በሰበብ አስባቡ ፣ ትግሉን ሰላፈነ
ከህዝቡ ማዕበል ፣ ከቁጣው የዳነ
አስመስሎ ቢያውጅ ፣ ሰላም የሰፈነ
        መሸነፉን አውቆ ፣ አብይ እንዳመነ
        ሽገር አይጠፋውም ፣ ውስጡ እንደቀዘነ ።

ንፁሃን ዜጎችን ፣ እያስወነጀለ
ስንቱን ያሳፈነ ፣ ስንቱን ያሰቀለ
በመለስ ተዘርቶ ፣ ኢንሳ የበቀለ
በስለላ ማፊን ፣ ጥርሱን የነቀለ
        ዛሬ ንጉስ ሆኖ ፣ ባፉ እየደለለ
        አገር ሲያፈራርስ ፣ ማን አለ ፣ ያስተዋለ ።

ኦነጋዊ አቀንቃኝ ፣ ተጓዥ ወደኋላ
በወሬ እያዋዛ ፣ ምኞቱን ሊያሟላ
መደመር እያለ ፣ በኬኛ የሚያሰላ
ጋዜጠኛ እስክንድር ፣ በቀየሰው መላ
        የአብይ ጦርነት ፣ የፈሪዎች ዱላ
        ፅንፈኛ አካሄዱን ፣ ቁማሩን ተበላ ።

ታዛቢው

March 30, 2019